# የዜግነት እና ህጋዊ የመስራት መብት

እንደ የሥራ አጥነት ዋስትና ጥቅሞች ብቁነት ሁኔታ፣ የፌዴራል ሕጎች እያንዳንዱ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ በሐሰት ምስክርነት ቅጣት ሥር የU.S. ዜግነት እንዳላቸው ወይም እንደሌላቸው እንዲገልጹ ይጠይቃል። የU.S. ዜግነት የሌለው ግለሰብ በU.S. ውስጥ የመሥራቱን ፈቃድ ለማረጋገጥ የውጭ ዜጋ ምዝገባ ሰነድን ማቅረብ አለበት።

የሥራ ስምሪት ደህንነት መምሪያ (Employment Security Department, ESD) የግለሰቦችን የስደት ሁኔታ በስልታዊ የውጭ ዜጎች ማረጋገጫ ለባለቤትነት መብቶች (Systematic Alien Verification for Entitlements, SAVE) በይነገጽ በኩል ያረጋግጣል። የ  የባለቤትነት መብቶች ስልታዊ የውጭ ዜጋ ማረጋገጫ ፕሮግራም SAVE በ U.S ዜግነት እና ኢሚግሬሽን አገልግሎቶች (U.S. Citizenship and Immigration Services ,USCIS) ይተዳደራል።

## እኔ የU.S. ዜጋ ካልሆንኩ ለስራ አጥነት ጥቅሞች ማመልከት እችላለሁን?

አዎ፣ የUnited States ዜጎች ያልሆኑ ለሥራ አጥነት ጥቅሞች ማመልከት ይችላሉ። የስደተኝነት ሁኔታዎን ለማረጋገጥ የውጭ ዜጋ ምዝገባ ሰነድዎን ለመምሪያው ማቅረብ አለብዎት። ይህ ሰነድ አብዛኛውን ጊዜ በማመልከቻው ጊዜ ይሰጣል። በማመልከቻው ሂደት ጊዜ ይህንን መረጃ ማቅረብ ካልቻሉ ከዚያ በኋላ ሰነዶቹን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

## በማመልከቻው ሂደት ውስጥ ምን እጠየቃለሁ?

የU.S ዜጋ ወይም የአሜሪካ ብሔር እንዳልሆኑ ካረጋገጡ የሚከተሉትን ይጠየቃሉ፡

- ባለፉት 24 ወራት ውስጥ በUnited States ውስጥ በሕጋዊነት የመሥራት መብት አጊንተው ነበር? እና፣
- በጣም የቅርብ ጊዜው የኢሚግሬሽን ሰነድዎ ምንድነው?
    - I-327 እንደገና ለመግባት ፈቃድ (I-327 Reentry Permit)
    - I-551 የቋሚ ነዋሪ ካርድ (I-551 Permanent Resident Card)
    - I-571 የስደተኞች የጉዞ ሰነድ (I-571 Refugee Travel Document)
    - I-766 የቅጥር ፈቃድ ካርድ (I-766 Employment Authorization Card)
    - I-94 የመድረሻ/የመነሻ መዝገብ (I-94 Arrival/Departure Record)
    - I-94 የመድረሻ/የመነሻ መዝገብ ጊዜው ባላለፈ የውጭ ሃገር ፓስፖርት ውስጥ
    - የስደተኛ ቪዛ
    - ጊዜያዊ I-551 ማህተም (በፓስፖርት ወይም I-94 ላይ)

## ጊዜው ባላለፈ የውጭ ፓስፖርት ውስጥ የI-94 የመድረሻ/የመነሻ መዝገብ አለኝ። ምን እንዳስገባ እጠየቃለሁ?

ጊዜው ባላለፈ የውጭ ፓስፖርት ውስጥ የI-94 የመድረሻ/የመነሻ መዝገብ ካለዎት የሚከተሉትን ማስገባት ይጠበቅብዎታል፡

- የፓስፖርት ቁጥርዎን፣
- የI-94 ቁጥርዎን እና
- ጊዜው የሚያበቃበት ቀን።

**ጊዜው ባላለፈ ነገር ግን ጊዜው የሚያበቃበት ቀን በሌለው የውጭ ፓስፖርት ውስጥ የI-94 የመድረሻ/የመነሻ መዝገብ አለኝ። ምን ላስገባ?**

ጊዜው ባላለፈ ነገር ግን በመግቢያ ጊዜዎ በ የአገር ውስጥ ደህንነት መምሪያ (Department of Homeland Security) እንደ የመቆያ ጊዜ (Duration of Stay, D/S) በመታተሙ ምክንያት ጊዜው የሚያበቃበት ቀን በሌለው የውጭ ፓስፖርት ውስጥ የI-94 የመድረሻ/የመነሻ መዝገብ ካለዎ፣ ጊዜው ካለፈበት ቀን ይልቅ I-94 የተፈጠረበትን ቀን ወይም የገባበትን ቀን ማቅረብ ይችላሉ።

አሁንም ትክክለኛ ፓስፖርት ካለዎት በፓስፖርትዎ ላይ የሚያበቃበትን ቀን ማስገባት ይችላሉ።

ይህ መመሪያ የተሰጠው በ Department of Homeland Security ነው።

**እኔ I-94 ከሌለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

የእርስዎ I-94 ቅጂ ከሌለዎት እዚህ የኤሌክትሮኒክ ቅጅ ለማግኘት የ Department of Homeland Security መጎብኘት ይችላሉ።

የእርስዎን የI-94 ኤሌክትሮኒክ ቅጂ ማግኘት ካልቻሉ፣ እዚህ ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ።

**እኔ ሰነድ የሌለኝ ሠራተኛ ነኝ። ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ ነኝ?**

በፌዴራል የኮሮናቫይረስ ዕርዳታ፣ የእርዳታ እና የኢኮኖሚ ደህንነትህግ (Coronavirus Aid, Relief, and Economic Security Act, CARES Act) መሠረት ለሥራ አጥነት ጥቅሞች እና ለተስፋፉ የሥራ አጥነት ጥቅሞች ብቁ ለመሆን በአሜሪካ ውስጥ ለመስራት ፈቃድ ሊኖርዎት ይገባል። ሆኖም ለክፍለ-ግዛቱ የተከፈለ የቤተሰብ እና የህክምና ፈቃድ ፕሮግራም (Paid Family and Medical Leave) ብቁነት ስናስብ የስደትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ አናስገባም። ስለዚህ በጠና ከታመሙ ወይም በጠና የታመመን ሰው የሚንከባከቡ ከሆነ ይህ ፕሮግራም ሊረዳዎ ይችላል። የበለጠ ለመረዳት paidleave.wa.gov ወይም tometiempo.org ይጎብኙ።

**የሥራ አጥነት ወይም የተከፈለበት የቤተሰብ/የሕክምና ፈቃድ ጥቅማጥቅሞችን ማግኘቴ በአዲሱ የሕዝብ ክፍያ ሕጎች መሠረት ለአረንጓዴ ካርድ ወይም ለዜግነት የማመልከት አቅሜን ያሰጋ ይሆን?**

አይ። የሥራ አጥነት ዋስትና እና የተከፈለበት የቤተሰብ እና የሕክምና ፈቃድ ጥቅሞች በሕዝብ ክፍያ ውሳኔ ውስጥ አይካተቱም።

የስራ ቅጥር ዋስትና መምሪያ እኩል ዕድል የሚሰጥ ቀጣሪ/ፕሮግራም ነው። አካል ጉዳተኞች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት አጋዥ መሳሪያዎችና አገልግሎቶች ይቀርባሉ። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስንነት

ላለባቸው ሰዎች የቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች ከክፍያ ነጻ ይቀርባሉ። የዋሽንግተን ማስተላለፊያ አገልግሎት (Washington Relay Service)፡ 711